

# ዳዊትና ዮናታን

* የንጉስ ልጅ የሆነው ዮናታን መልካምና ደግ ልጅ ነበር። የዳዊትም እጅግ በጣም ጥሩ ጓደኛው ነበር። ምንም ነገር ቢመጣ ሁልጊዜ ጓደኛሞች እንሚሆኑ እርስ በርሳቸው ቃል ተገባቡ።

* ዳዊት ቤተ መንግስቱን ለቆ ለመሄድ ወሰነ። ንጉስ ሳኦል ይገድለኛል ብሎ በጣም ፈራ። ዮናታን ግን ዳዊት እንዲሄድበት አልፈለገም። “አባቴ አይጎዳህም፣ሁልጊዜ ማድረግ የሚፈልገው ነገር ካለ ለእኔ ሳይነገረኝ አድርጎት አያውቅም።”አለው።

* ሆኖም ዳዊት ፍርሃቱ አልለቀቀውም። በአደጋ ላይ እንዳለ በትክክል ተገንዝቦአል። ንጉስ ሳኦል ዳዊትን መጥላት ጀምሮአል። ሳኦል ልጁን ዮናታንን ዳዊትን እንዲገድለው አዘዘው። ሆኖም ዮናታን ዳዊትን እጅግ በጣም ስለሚወደው ዳዊትን ለማዳን እቅድ አወጣ። እንዲህም ሲል ለዳዊት ነገረው “ከዚህ በማይርቅ ሜዳ ላይ አንድ ድንጋይ አለ። ሄደህ ከዚህ ድንጋይ ኋላ ተደበቅ።ከሶስት ቀን በኋላም ከአገልጋዬ ጋር መጥቼ ሶስት ቀስት ወደኢላማ እወረውራለሁ። ከዚያም አገልጋዬን ‘ሄደህ የወረወርኩትን ቀስት አምጣ፣ ፍላፃው ከአንተ ወደዚህ ነው። አምጣልኝ’ ካልኩት ሁሉ ሰላም እንደሆነና ምንም የሚያሰጋ ነገር እንደሌለ ትረዳለህ። ፍላጻው ከአንተ ወደዚያ ነው፤ ይዞኸው ወደ እኔ ና ያልሁት እንደ ሆነ፥ ሕያው እግዚአብሔርን! ለአንተ ደኅንነት ነውና ምንም የለብህም። ሆኖም ‘ፍላጻው ከአንተ ወዲያ ነው’ ካልኩት ግን በእርግጥ አደጋ አለ። ስለዚህ ሽሽ።”

ስለዚህ ዳዊት በሜዳው ውስጥ ተደበቀ። ዮናታን ወደ ንጉስ ሳኦል ዘንድ ሄደ።  ዳዊትን እንዳይገድለው ለመነው። ንጉስ ሳኦል ዮናታንን ለመስማት ፈቃደኛ አልነበረም። እንዲያውም አጅግ ተቆጣ።  ጭራሽ ሰይፉን ወደዮናታን ወረወረበት። ሳተው እንጂ።

* ዮናታን  ከቤተ መንግስቱ አገልጋዩን ይዞ በፍጥነት ዳዊት ወዳለበት ሜዳ ሄደ። ወዲያውም ፍላፃዎቹን ወረወረ። አገልጋዩንም "የወረወርኩትን ፍላፃ አምጣልኝ። ከአንተ በኋላ ነው።" አለው።

* ዳዊትም እጅግ አዘነ።  አገልጋዩም ፍላፃውን ይዞ ተመለሰ።  ዮናታንም አገልጋዩን ወደ ቤተ መንግስት መልሶ ላከው።  ዳዊትም ከደበቀበት ወጣ። ዮናታንን ጥምጥም አድርጎ አቀፈው።
አባቱ ሊገድለው እንዳሰበና በተቻለው መጠን ለደህንነቱ ሲል ራቅ ወዳለ ቦታ እንዲሄድ መከረው። ዳዊትንም የሁልጊዜ ጓደኛው እንደሆነ እንዲያስታውስ ነገረው።

* ዳዊትም ሸሸ። በምድር በዳም አንድ ዋሻ አግኝቶ በዚያ ለረጅም ጊዜ ኖረ።

የዳዊትና የዮናታን ወዳጅነት ታሪክ የሚገኘው በመፅሐፈ ሳሙኤል ምዕራፍ 20 ውስጥ ነው።

http://gardenofpraise.com